# ኃይማኖትንና ፖለቲካን አደበላልቆ ማቡካት

ጡሃ ሙዘይን

ትግራይ ኦንላይን April 21, 2014

ሃይማኖትና እምነት በልቦና የሚይዙትና በፈቃደኝነት የሚከተሉት ግለሰባዊ ረቂቅ ሃብት ነው፤ በተቃራኒው በየአደባባይ እየዘረጉ የሚቸበችቡት የገበያ ሸቀጥ ግን አይደለም። አምላካችንስ ቢሆን ‘ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ኑሩ’ አለ እንጂ በእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ታበዩ መቼ አለና! እንዲያ ብሏል እንዴ - ኧረ በጭራሽ። ሆኖም ለዚህኛው አሊያም ለዚያኛው ኃይማኖት ህልውና ከኛ ወዲያ ላሳር ባዮችን አሁን...አሁን አዲስ ነገር አይደለም፤ በየሄዱበት እየተለመደ መጥቷል፡፡ እነዚህን ወገኖች የየትኛውም እምነት አስተምህሮት አይደግፋቸውም፡፡ አብሮ ለመኖር ሰው ሆኖ መፈጠር ብቻ በቂ በሆነባት ዓለማችን ጥቂቶች የግል ፍላጎታቸውን በሌላው ላይ ለመጫን ሲሯሯጡና የሌላውን ኃይማኖታዊ ማንነት ለመደፍጠጥ ሲውተረተሩ ማየት ከልብ ያሳዝናል፡፡

ስለ እምነት ጉዳይ ሊቃውንትን ጨምሮ ጠቢባን ከዚያም እልፍ ሲል ተራውም ሰው ጭምር ብዙ ብለዋል፤ ጽፈዋል፣ ሰብከዋል — ትናንት ሆነ ዛሬ። ወደፊትም ብዙ ይላሉ፡፡ አያሌ ፀሐፍት በዚህ ዙሪያ ብዙ...ብዙ ብለዋል። ፖለቲከኞች ብዙ ደስኩረዋል - “አንድ ኃይማኖት፣ አንድ ሀገር” እያሉም አቀንቅነዋል፡፡ በሌላኛው ጫፍ መንግሥት በኃይማኖታዊ ሥርዓት እንዲመራ የሚዳዳቸውም አልጠፉም፡፡ መቼም ሰው አፈጣጠሩ ለየቅል ነውና አንድ ወጥ አቋምና አመለካከት እንዲይዝ ወይም ተመሳሳይ ስብዕና እንዲኖረው መጠበቅ የዋህነት ነው፡ ይህ እንዲሆን አይጠበቅም፤ አይቻልምም — ልዩነቱ ተፈጥሮዓዊ ነውና፡፡ ያም ቢሆን ግን ያፈጠጠና ያገጠጠ አፈንጋጭነት የሌለውን ማንነት የማዳመጥ አባዜ ከእውነታው ዓለም ጋር የሚላተም አጉል ቂላቂልነት ነው — በምድር ሆነ በሰማይ ተቀባይነት የሌለው ተላላነት ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ ‘የእኔ አስተሳሰብና እምነት ከማንም የላቀ ነው’ እያሉ በአደባባይ የሌላውን እምነት የሚያጣጥሉ ጊዜ ያለፈባቸው ኋላ ቀር አስተሳሰብ አቀንቃኞች ነገረ ሥራ እጅጉን ይገርማል፤ ይደንቃልም፡፡ ለዚያውም በዚህ አብሮነት የግድ በሆነበት ዘመናዊ ዓለም ውስጥ ራስን ከፍ በማድረግ ሌላውን አሳንሶ ማየትና እምነቱንና ማንነቱን ማናናቅ ተገቢ ያልሆነ ብቻ ሳይሆን መያዣና መጨበጫ የጠፋው እሳቤ ነው ማለት ይቀላል፡

ብዙኃኑን ምዕመን ማለትም ህዝበ ክርስቲያኑንና ህዝበ ሙስሊሙን ወክለው ራሳቸውን የኃይማኖትና የፈጣሪ ጠበቃ አድርገው የሚቆጥሩ ኃይማኖትንና ፖለቲካን ደበላልቀው ሊሸቅሉ የሚቆምሩ የእምነት ሲራራ ነጋዴዎች እኩይ ሴራቸው ከምን እንደሚመደብ ግራ ግብት ይላል፡፡ እነዚህ ጥቂት ግለሰቦች አቁማዳቸው ሲጎድል፤ ኪስ እና ኮሮጆአቸውን ለመሙላት ሲሉ በኃይማኖት ጓዳ ይደበቃሉ፤ እነዚህ የተሸሸጉ ቁማርተኛ ፖለቲከኞች መሆናቸውን ልብ እንበል፡፡ ያም ሆነ ይህ በክርስትናም ይሁን በእስልምና ኃይማኖቶች ውስጥ እምነትን ሽፋን በማድረግ የሚካሄዱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን አንድ በአንድ እንፈታትሻቸው።

በክርስትና ኃይማኖት ሽፋን የሚካሄደው እንቅስቃሴ በዋነኛነት “ኢትዮጵያ የክርስትና ኃይማኖት የበላይነት ሊነግስባት ይገባል” በሚል ማጠንጠኛ ኋላ ቀርና ዘመን የሻረው አስተሳሰብና ኃይል የሚመራ ነው፡፡ ይህ ኋላ ቀር ኃይል መነሻና መድረሻውን የክርስትና ኃይማኖትን የበላይ አድርጌ ‘ይህን ሊያረጋግጡልኝ፣ ህዝበ ክርስቲያኑንም ሊያነሳሱልኝ ይችላሉ’ የሚላቸውን መፈክሮች ቀዳሚ አድርገው ይዘው ይነሳሉ፡፡ “ኢትዮጵያ የክርስትና ደሴት ነች፣ አንድ ሀገር አንድ ኃይማኖት” የሚሉ መፈክሮቹ የአስተሳሰቡን ጭብጥ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በዚህ ኃይል አስተሳሰብ መሠረት ሀገራችን በርካታ ኃይማኖቶችን ያስተናገደችና

በማስተናገድ ላይ የምትገኝ ሀገር መሆኗ ይዘነጋ፤ እሱ ይቀርና የክርስቲያን ደሴት ብቻ ተደርጋ ትቀርባለች፡፡ ይህ ደግሞ የሌላውን የኃይማኖት እኩልነትና የእምነት ነፃነትን በጠራራ ፀሐይ ገፍቶ የሚጥል ነው።

ሁሉንም ጉዳይ እንተወውና "አንድ ሀገር፣ አንድ ኃይማኖት" የሚለው አስተሳሰብ በራሱ ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ኃይማኖት ብቻ እንዳለ ወይም ሊኖር እንደሚገባ የሚሰብክ ኋላ ቀር የፀረ እኩልነት አስተሳሰብ ነው፡፡ ከእነዚህ ኃይሎች ውስጥ አንዳንዶቹ የኃይማኖት ጉዳይ ዜጋን በቀላሉ ሊያደናግርልን ይችላል ብለው የሚያምኑ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ከፊሎቹ ደግሞ ከኃይማኖት አኳያ የኦርቶዶክስ እምነት መንግሥታዊ ኃይማኖት መሆኑ ቀርቶ ከሌሎች ኃይማኖቶች ጋር በእኩልነት የሚታይና የሚከበር መሆኑን ያልተቀበሉና በትናንቱ ዓለም ትዝታ የሚኖሩ፤ በራሳቸው የህልም ዓለም ውስጥ ሰጥመው የቀሩ፣ ከእንቅልፋቸው ገና ያልባነኑ ናቸው። ታዲያ እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የክርስትና ኃይማኖትን መጠለያ በማድረግ የተለያዩ ቀስቃሽና ስሜትን የሚኮረኩሩ የፈጠራ አጀንዳዎችን ለማራገብ ይሞክራሉ፡፡ ከእነዚህ ሙከራቸው ውስጥ ጥቂት አብነቶችን እንጠቃቅስ፤ መንግስሥት በኃይማኖት አባቶች ሹመት ላይ እጁን ያስገባል፣ የዋልድባ ገዳም ተደፈረ፣ አልፎ...አልፎ በአጋጣሚ ቤተክርስቲያን ባለበት አካባቢ ከድርቅ ጋር ተያይዞ የተነሳን ቃጠሎ ሆን ተብሎ እንደተፈፀመ አስመስሎ የአሸባሪው ግንቦት ሰባት ልሣን በሆነው ኢሣት እንዲሁም በጨለምተኞቹ የአሜሪካን ድምጽ ራዲዮ ዘጋቢዎች በኩል በማስወራት ጉዳዮቹ እውቅናና ትኩረት እንዲያገኙ ሀሰተኛ ጩኸት ማስተጋባት አንደኛው ሥልታቸው ነው፡፡

በራሳቸው ፖለቲካዊ መሥፈርት የቤተ ክርስቲያኒቱን መሪዎችና ኃላፊዎች መሾምና መሻር የሚፈልጉት እነዚህ ህልመኞች በተለይም በውጭ የሚገኙ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች የራሳቸውን ሰው አዘጋጅተው ለማስመረጥ ያለደረጉት ጥረት አልነበረም። በተለይም የዋልድባ ገዳም እንደተደፈረ አስመስለው የነዙት አሉባልታ አስገራሚ ነበር። ግና አሉባልታቸው መሠረተ ቢስ ነውና አልሰመረላቸውም። በተለያዩ አካባቢዎች የሚካሄዱ የስኳር ልማት ሥራዎችን በተመለከተም ብዙ...ብዙ አፍራሽ ወሬዎችን ነዝተዋል፡፡

በገዳሙና በስኳር ማሣው መካከል ያለውን ከፍተኛ የመልክዓ ምድር ልዩነት በቅርቡ ለማያውቁ የክርስትና ምዕመናን ሁሉ 'ገዳሙ ተደፈረ' የሚለው ቃል እልህና የቁጣ ስሜት ይፈጥርባቸዋል ብለው በማመን ሰፊ ዘመቻ ሲያካሂዱ ከርመዋል፡፡ እዚህ ላይ የዘመቻው ፊታውራሪዎች በአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ጣቢያ የአማርኛው ክፍል ውስጥ የሚገኙ የቀድሞ እነዚያው ጨለምተኞች፣ የጋዜጠኝነትን ካባ ያጠለቁ ጽንፈኞች መሆናቸውን ልብ እንበል፡፡

ሌሎች አብነቶችንም እንጨምር። በአንድ ወቅት በምዕራብ ኢትዮጵያ ጅማ አካባቢ በ"ኻዋርጃ" ስም የሚታወቁ አክራሪዎች በክርስቲያኖች ላይ ያደረሱትን ግድያ መጠጊያ በማድረግ "ክርስቲያኖች እየተጨፈጨፉ ነው፣ ስለዚህ አፀፋ ሊሰጠው ይገባል" በሚል ቅኝት መንቀሳቀስ ጀምረው ነበር፡፡ አልፎ...አልፎ እንደምናየውም ከድርቅ ጋር በተያያዘ ምክንያት በሚነሳ ቃጠሎ አንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም ገዳም ባለበት አካባቢ በአጋጣሚ ቃጠሎ ከተነሳ፤ ይህንኑ ሆን ተብሎና በክርስትና ላይ ጥቃት ለመፈፀም ሲባል እንደተደረገ አስመስሎ የማቅረብ ዘመቻ ነበረ፡፡ እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን መሰሪያ ተብሎ ባልተሰጠ ቦታ የቤተክርስቲያን ግንባታን ሆን ብሎ መጀመርና ኋላ ላይ ህገ ወጡ ግንባታ እንዲቆም ሲጠየቅ "በክርስትና ኃይማኖት ላይ ተዘመተ" ብሎ የእኩልነት ጥያቄ ማንሳት አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የተበሉና ጊዜ ያለፈባቸው ሥልቶች ነበሩ ወይም ናቸው፡፡ ሆን ተብሎ ግጭትን ለማነሳሳት በሚቋምጡ ብሎም የተሳሳተ አስተሳሰብ ባላቸው ዜጎች የሚራመዱት እነዚህ ኋላ ቀርና ፀረ ሠላምና እኩልነት አስተሳሰቦች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ኃይማኖታዊ አዝማሚያ ባልተለያቸውና በመንግሥታዊ ኃፊነትና በእምነታቸው መካከል ያለውን ልዩነት በውል መገንዘብ የተሳናቸው ኃላፊዎች ደግሞ የየራሳቸውን ስህተት ሲሰሩ ተስተውሏል፡፡

ድርጊቱ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በኃይማኖት ጓዳ ውስጥ የተወሸቁት ፖለቲኞች በወቅታዊና ለፖለቲካ ንግድ የሚያመች እንዲህ ዓይነት አጀንዳ ሲፈጠር አጋጣሚውን ለመጠቀም ምን ጊዜም ወደ ኋላ አላሉም፡

፡ እናም በክርስትና ስምና ሽፋን የሚነግዱ ፖለቲከኞች አነዚህን የመሳሰሉ መሠረተ ቢስ አጀንዳዎችን በመቅረጽና በማራገብ ክርስትና ኃይማኖት ተከብሮና ተቻችሎ በሚኖርባት አዲሲቷ ኢትዮጵያ ውስጥ የእምነቱ ክብርና ሞገስ የተገፈፈ አስመስለው ማቅረባቸው የተለመደ ተረት ተረት ጨዋታቸው ሆኗል፡፡ ታዲያ ለእምነቱ ክብርና ሞገስ የሌላቸውና ራሳቸውም ቢሆኑ በኃይማኖቱ ሽፋን የፖለቲካ ንግድ የሚያካሂዱት ኃይሎች መሆናቸውን ደብቀው መንግሥትና ሥርዓቱን በመሠረተ ቢስ ወንጀል እየከሰሱ መኖርን ሥራዬ ብለው መያያዛቸውን ማንኛውም የክርስትና እምነት ተከታይ ሊገነዘበው ይገባል፡፡

ወደ እስልምና እምነት ጉዳይ እናምራ፡፡ በእስልምና ኃይማኖት ውስጥ ወደሚገኙት የፖለቲካ አንቀሳቃሽ ኃይሎች ስናመራ ደግሞ በክርስትና ኃይማኖት ሽፋን ከሚካሄደው እንቅስቃሴ ባልተናነሰ እንዲያውም አልፎ...አልፎ በራሱ ባህሪ ሳቢያ ከዚያም በከፋ ሁኔታ በእስልምና ኃይማኖት ስም ኃይማኖታዊ ፖለቲካ መካሄዱ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ታዲያ ይህ እንቅስቃሴ ውስጥ ውስጡን ሲካሄድ ቆይቶ፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አክራሪነትን ለመታገል እንቅስቃሴ ሲጀመር በግልፅ ፀረ ህገ መንግሥታዊ መልክ ይዞ መታየት መጀመሩ ሁኔታዎችን በጥሞና ለሚከታተል ማንም ዜጋ ግልጽ ነው፡፡

ከዛሬ 23 ዓመታት በፊት በጨቋኙ ሥርዓት ይደርስባቸው ከነበረው ግፍና በደል በዴሞክራሲያዊ ትግል ተላቀው የኃይማኖታቸውን እኩልነት ባስከበሩባት አዲሲቷ ኢትዮጵያ፤ የኃይማኖት የበላይነትን በማስፈን ቅኝትና ከሌሎች ኃይማኖት ተከታይ ወንድሞቻቸው ጋር በመቻቻልና በእኩልነት የመኖር ዕድልን በሚዘጋ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ አክራሪ ዝንባሌዎች መታየታቸው አልቀረም፡፡

እነዚህ እንቅስቃሴዎች በዋኛነት ምንጫቸው ከሰሜን አፍሪካና ከመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች አክራሪ ኃይሎች ነው፤ በአንድ በኩል የእስልምናን የበላይነት በአካባቢያችን ለማስፈን የሚካሄደው ዕቅድ ማስፈፀሚያ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኃይማኖቱ በሚነግዱ ግለሰቦችና ቡድኖች በሀገሪቱ የተፈጠረውን የእኩልነት ሥርዓት በመፃረር የበላይነትን ለማስፈን የሚካሄደው እንቅስቃሴ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ታዲያ በእነዚህ አክራሪ አስተሳሰቦች የሚመሩ ፅንፈኞች መንግሥት በኃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ በመገንዘብ በኃይማኖት ሽፋን የዜጐችን ሰብዓዊ መብቶች የሚረግጡ በርካታ አስነዋሪ ተግባራትን ፈጽመዋል፡፡ በአደባባይ የኃይማኖት አባቶችን ገድለዋል፤ አዋርደዋል፤ ነባር መስጊዶችን አቃጥለዋል፤ ኢትዮጵያዊ መሠረት አላቸው የሚሏቸውን የኃይማኖት መጽሐፍትንም አቃጥለዋል፡፡

ይህን በመቃወም ድርጊቱን ለማስቆም የሞከሩ ዜጐችን፣ የኃይማኖት ትምህርት ቤቶችንና መስጊዶችን እንዲሁም የአመራር ቦታዎችን በጉልበት ነጥቀዋል። ድርጊቱን የተቃወሙ ዜጐችን ሁሉ ከቤት ንብረታቸው አፈናቅለዋል፡፡ እነዚህ ተግባራት ከሞላ ጐደል አክራሪዎቹ በደረሱባቸው ቦታዎች ሁሉ ያካሄዷቸው ናቸው፡፡ ለነገሩ የአክራሪዎቹ የመጀመሪያ ሙከራ ያነጣጠረው በኢትዮጵያ ያሉ ብዙዎቹ ነባር ኃይማኖቶች ሁሉ መሠረታቸው መካከለኛው ምሥራቅ መሆኑ እየታወቀ 'መንግሥት አህባሽ የሚባል ኃይማኖት ከውጭ አመጣብን' የሚል ነው። ግና ይህ መከራከሪያ ውኃ የማይቋጥር ቢሆንም መንግሥት ይህኛውን ወይም ያኛውን ኃይማኖት ከዚህኛው ወይም ከዚያኛው ሀገር በኩረጃ ሆነ በትዕዛዝ የሚያመጣበት ምክንያትም ሆነ አመክንዮ አልነበረውም፤ የለውምም፡፡ አላደረገውምም፡፡

ሀቁ ይህ ሆኖ እያለ በውጭ ገንዘብ ድጐማ የሚንቀሳቀሱት እነዚህ ኃይሎች ባላቸው አቅም ሁሉ እየታገዙ መንግሥት በሐጂ አብዱላሂ መምህርነት የተስፋፋውን አህባሽ የሚባል የውጭ እምነት አምጥቶ ሙስሊሙን ኅብረተሰብ ሊጭንበት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል የሚል መሠረተ ቢስ ወሬዎችን እያናፈሱ መንግሥት በኃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ገባ በማለት መሠረተ ቢስ ክስ ሲያሰሙ ሰንብተዋል። በዚህም በተለይም ወጣት የሆነውን የሙስሊም ምዕመን ለማደናገር ሞክረዋል።

የአስተምህሮ መሠረታቸው ብቻ ሳይሆን የፋይናንስ ምንጫቸውም የውጭ ኃይል፣ ለዚያውም ከመካከለኛው ምሥራቅ በሆነበት ሁኔታ መንግሥትን በኃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ገብነት ለመክሰስ

የሚያስችላቸው ሞራላዊ ብቃት እንዴት ሊጐናፀፉ ቻሉ? የሚሰጣቸውን የገንዘብ ድጋፍ በመጠቀም ነባሩን የሱፊ እምነት ለመገለባበጥ ያደረጉት ጥረትና በተወሰነ ደረጃ ያገኙት ውጤት የልብ ልብ ስለሰጣቸው ብቻ ራሳቸውን ምሉዕ በኩልሄ ሀገር በቀል ምዕመን፣ ሌላውን ደግሞ መጤ ለማስመሰል እስከ መሞከር ደርሰዋል፡፡ በጣሙን ያሳዝናል፤ ያሳፍራልም፡፡

ደግነቱ በዚህች ዴሞክራሲያዊት ምድር ሀገር በቀል መሆን ወይም አለመሆን እምነትን ለማስተማር ቦታ የሌለው መሆኑ በጀ እንጂ፤ ሀገር በቀል ያልሆነ እምነት ሁሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ቦታ ሊኖረው አይገባም ቢባል ማን ወጥቶ ማን ይቀር ይሆን? ዳሩ ግን አዲሲቱ ኢትዮጵያ የኃይማኖት መለኪያዋ የዜጐች ምርጫ መሆን አለመሆኑ ብቻ ነው — መሠረቱ ኢትዮጵያዊ፣ አፍሪካዊ ወይም የሌላ ዓለም መሆን አለመሆኑ አይደለምና። ሀገራችን ከመካከለኛው ምሥራቅ አንዳንድ ሀገሮች በቅርቡ የገቡትን ሌሎች አስተምህሮዎች እንዳልከለከለች ሁሉ አህባሽንም ሆነ ሌላ አስተምህሮ የዜጐች ምርጫ እስከሆነ ድረስ እንዳይገባ የምትከለክልበት ምክንያት ሊኖራት አይገባም፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ መንግሥት ጉዳዩን አቃሎ በመመልከት ሰፊና አጥጋቢ ማብራሪያ ባለመስጠቱ አክራሪዎቹ ፈቃጅና ከልካይ ሆነው አህባሽ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የለበትም የሚል አስተምህሯቸው የብዙዎቹን ወጣት ሙስሊሞች አዕምሮ እንዲበርዝ ዕድል ሊያገኝ ችሏል፡፡ እነዚህ አክራሪዎች ሌላው መጠቀሚያ ሊያደርጉት የሞከሩት የአወሊያ ትምህርት ቤትን ጉዳይ ነው፡፡ እርግጥ መንግሥት ከትምህርት ቤቱ የፈለገው ኃይማኖትና ፖለቲካ የተነጣጠሉ መሆናቸውን በመቀበል፤ ከማናቸውም ዓይነት የፖለቲካ አስተምህሮ በፀዳ አኳኋን ተግባሩን እንዲፈጽም ብቻ ነው፡፡ ግና ተቋሙ ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አክብሮ ከመንቀሳቀስ ይልቅ፤ ለማንም ተጠያቂነት በሌላቸው ወገኖች እየተመራ ከኃይማኖታዊ ጉዳዮች በራቁና ለአክራሪዎች በተመቹ አጀንዳዎች ተጠምዶ ጊዜውን ሲያሳልፍ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ይህንኑ መነሻ በማድረግ ድርጅቱ በእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የሚመራና ተጠያቂነት ያለበት ተቋም እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በወቅቱ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከየአቅጣጫው በሚነሱ ጥያቄዎቹ አማካይነት የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤቶችን እንደ አዲስ መርጦ ማደራጀት እንደሚፈልግ ግልፅ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቶቹ በአፋጣኝ በሚካሄድ ምርጫ እንዲዋቀሩ ጥያቄ አቅርቦ ነበር፡፡ ጥያቄው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ህገ መንግሥታዊ መብት በመሆኑ፤ መንግሥት ይህንኑ ተቀብሎ ምክር ቤቶቹ ለዚህ የህዝብ ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ እንዲሰጡ የሚጠበቅበትን ምክር ለግሷል፡፡ ምክር ቤቶቹ በአፋጣኝ በሚካሄድ ምርጫ እንዲዋቀሩ የማድረጉን ዴሞክራሲያዊ አሠራርም ደግፏል፡፡ ይሁንና አክራሪዎቹ ልክ መንግሥት ጣልቃ እንደገባና ያለ ሙስሊሙ ህዝብ ፍላጐት መራጮች በላዩ ላይ እንደተጫኑበት በማስመሰል ሲቀሰቅሱ ቆይተዋል፡፡ ከዚህ ታላቅ የዴሞክራሲ ተግባር አቋርጠው በመውጣት ራሳቸውንም አግልለዋል፡፡ በውጤቱ ግን ህዝቡ ከአክራሪነት የፀዱ የሚላቸውን ሰዎች መምረጡን አረጋግጧል፡፡ ዳሩ ግን አክራሪዎቹ የህዝቡን ምርጫ ወደ ጎን በማለት "ድምፃችን ይሰማ!" በማለት ሰርክ አርብ ዕለት በአንዋር መስጊድና አልፎ...አልፎም በሌሎች መስጊዶች ከመንግሥት ጋር በከፍተኛ ደረጃ ሲፋጠጡ ከርመዋል፡፡ ዛሬ ላይ ሁኔታው ትንሽ የተቀዛቀዘ በሚመስልም፡፡

ከውጭ ሚዲያዎች ጋር በተቀናጀ አኳኋን በእስልምና ኃይማኖት ላይ ጥቃት የደረሰ በማስመሰል ለማነሳሳትም በርካታ ጥረቶችን አድርገዋል፡፡ ጉዳዩ በፖሊስና በፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ትዕግስት መላበስ ምክንያት ወደ መካረርና ግጭት እንዳይመራ ተደረገ እንጂ፤ ከሞላ ጐደል ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል አክራሪዎቹ መንግሥትን ወደ ግጭትና ደም መፋሰስ ለማስገባት ያላደረጉት ጥረት አልነበረም፡፡ ለአብነት ያህል በአፍሪካ ህብረት ዓመታዊ ስብሰባ ወቅት ያልተፈቀደ ሰልፍ ለማድረግና የአዲስ አበባን መንገዶች በመዘጋጋት አደጋ ለመፍጠር ሙከራ ማድረጋቸው የዚህ አባባል ሁነኛ አስረጅ ነው፡፡ ባለፈው ክረምት አንድ ሌሊት ላይ ከቢላል መስጊድ በመነሳት አዲስ አበባ ከተማን ለማተራመስ መሞከራቸውም እንዲሁ፡፡ ታዲያ እነዚህ ኃይሎች ራሱን "ጀሃዳዊ ሃረካት" በሚል ስያሜ ለማስተዋወቅ ጥረት ያደርግ ከነበረ

የአሸባሪዎች ድርጅት ጋር በመቀናጀትም በአንዋር እና በሌሎች መስጂዶች ላይ መሰል የነውጥ ሙከራዎች በሽፋንነት መጠቀም መርጠው ነበር፡፡

ይህም ሆኖ ግን መንግሥት ረዥም ጊዜ ወስዶ ባካሄደው ጥናትና በሰበሰባቸው ማስረጃዎች ላይ በመመስረት በቡድኑ ቀንደኛ መሪዎች ላይ ህጋዊ ሥርዓቱን ተከትሎ የእሥራት እርምጃ ለመውሰድ ተገድዷል፡፡ እንግዲህ ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው የአክራሪዎቹ እንቅስቃሴ  በከፍተኛ ፍጥነት የመዳከም ሂደት ውስጥ የገባው፡፡ በሌላ በኩልም ኃይማኖትን በሽፋንነት ለመጠቀም የሞከረው ይኸው ኃይል፤ በተለይም በውጭ ከሚገኙ ደጋፊዎቹ ጋር በመቀናጀት አሉ የተባሉትን ፀረ ኢትዮጵያ ሚዲያዎች ከመጠቀሙም ባሻገር ከግንቦት 7 እስከ ስደተኛው ሲኖዶስ ድረስ ባሉ የሽብርና የትምክህት ኃይሎች ለመደገፍና ብርቱ ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህም “የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው” በሚል ፈሊጥ እርስ በእርስ ተሳስረውና ተደጋግፈው ሲንቀሳቀሱም ቆይተዋል፡፡ በጥቅሉ በኃይማኖት ሽፋን የሚካሄዱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውለው አድረው እየተጋለጡና እየተዳከሙ መሄዳቸው ባይቀርም፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመፈታተን ከሞከሩት ውስጥ ዋነኞቹ የሁከት ኃይሎች መሆናቸው የሚካድ አይደለም፡፡

እነዚህ በፖለቲካው መስክ ከስረው በአክራሪ ኃይማኖተኛነት የሚንቀሳቀሱት ኃይሎች ለምን ኃይማኖትን በሽፋንነት እንደመረጡ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። ሁሉም እንደሚያውቀው ኃይማኖትን በሽፋንነት በመጠቀም የፖለቲካ እንቅስቃሴውን ማካሄድ የመረጡት ኃይሎች የተለያየ መጠሪያ አላቸው፤ በመሠረታቸው ግን የትምክህት ወይም የጠባብነት መፈክሮችን አንግበው ለመፋለም የሞከሩ የፖለቲካ ኃይሎች ናቸው፡፡ ከቅንጅት እስከ ህብረት፣ ከቪኦኤ እስከ ቲቪ አፍሪካ፣ ከጀርመን ድምጽ እስከ ቢላል ራዲዮ፣ ከጀሃዳዊ ሃረካት እስከ ግንቦት ሰባት፣ ከኢትዮጵያ ሙስሊሞች ዓለም አቀፍ እስከ መድረክና እስከ ስደተኛው ሲኖዶስ ድረስ ያሉ ኃይሎች በተናጠልና በህብረት የተሳተፉበት ነው፡፡ ይሁንና ሁሉም ያነገቡትን ዓላማ በተለያዩ ፀረ ህገ መንግሥታዊ ሥልቶች በመታገዝ ቀቢፀ ተስፋቸውን ለማስፈፀም ሞክረው የከሸፈባቸው ኃይሎች መሆናቸው የዚያኑ ያህ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡

‘እነዚህ ዓላማቸውን በሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ በማራመድ ለስኬት መብቃት ያቃታቸው ድርጅቶችና የፖለቲካ ኃይሎች በኃይማኖት ሽፋን የከሸፈ ዓላማቸውን ማራመድ የመረጡት፤ ይህ ሥልት ምን ዓይነት ዕድል ቢሰጣቸው ነው?’ የሚል ጥያቄ ማንሳትና ጉዳዩን መመርመር ተገቢነት ይኖረዋል። በምላሹም በድሃና ኋላ ቀር ኅብረተሰብ ውስጥ በእምነት ጉዳይ ዜጐችን ብዥታ ውስጥ መክተት ለመረጡ ወገኖች በቀላሉ ያለመጋለጥ ዕድል ያጐናፅፈናል የሚል ሊሆን ይችላል።በአናቱም ለድል ያበቃናል ብለው ማሰባቸውና እልፍ ሲልም መደምደማቸው ነው፡፡ ያለ ምክንያት አይደለም - የእምነት ጉዳይ ለሚዛናዊ አስተሳሰብ ያለው ተጋላጭነት በተነፃፃሪ አነስተኛ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ስለሆነም ጭምር ነው፡፡ “በእምነትህ የመጣ ነው” ተብሎ የቀረበለትን ጉዳይ ሳያጣራ ያለማንገራገር ተቀብሎ ወደ ድርጊት ማምራት በብዙ የኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚታይ ክስተት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ አካሄድ በኃይማኖታቸው ቀናዒ የሆኑ ሰዎች በኃይማኖት ሽፋን የሚራመዱ የፖለቲካ አጀንዳዎች ሰለባ ለማድረግ የተሻለ ዕድል ይፈጥርልናል በማለት የተያዘ ለመሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በበለፀገው ዓለምም ቢሆን በአሸባሪነትም ሆነ በፀረ አሸባሪነት ጐራ ተሰልፈው የሚፋለሙ ኃይሎች ኃይማኖታዊ ጥሪ በማስተላለፍ የፖለቲካ ዓላማቸውን በኃይማኖት ግጭት መልክ ሲያስኬዱ ማየት የተለመደ ነው፡፡

የኃይማኖት ጉዳይ የትኛውንም ጎራ በመሠረተ ቢስ እምነት ነክ ውንጀላዎች በቀላሉ በስሜት በማነሳሳት ሌላውን እንዲጥሙ ማድረግ ይቻላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የከሰሩ ፖለቲከኞች ሁሉ ኃይማኖትን በሽፋንነት በመጠቀም መንቀሳቀሳቸው የእምነት ጉዳይ ለሚዛናዊ አስተሳሰብ ያለው ተጋላጭነት በተነፃፃሪ አነስተኛ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ መሆኑን ለመገንዘብ አይከብድም፡፡ ግና በኃይማኖት ስም የሚካሄደውን ንግድ ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ ረገድ አጋዥ ሚና የሚጫወቱ ችግሮች መኖራቸው አይቀርም፡፡

በዚህ ረገድ የድህነት መንሰራፋትና የመልካም አስተዳደር እጦት ወይም ጉድለት ተጠቃሽ ናቸው። በተጨባጭ እንደሚታየው በበለፀገና ሰርቶ የመጠቀም እድል በሰፋበት ማኅበረሰብ ውስጥ ለጽንፈኝነት መሠረት የሚሆን ተስፋ መቁረጥ አይገኝም፡፡ ሰርቶ መከበርና ማደግ ስለሚቻል ለተስፋ መቁረጥ ምክንያት የሚሆን ችግር አይኖርም፡፡ እነዚህን ችግሮች አሁን እየተሰራው ካለው በላይ በመቅረፍ ሊፈጠሩ የሚችሉ ቀጣይ ተግዳሮቶችን መቀነስ ብሎም ማስወገድ እንደሚቻል የመንግሥት ቀዳሚ ተሞክሮዎች ያረጋገጡት እውነታ ነው፡፡ በመሆኑም ውስጣዊ ተጋላጭነትን ዘርዝሮ ተገቢ ርምጃዎችን መውሰድ የሚገባ ይሆናል።

የተጀመረውን ፀረ ድህነትና ፀረ ኋላ ቀርነት ትግልንም ይበልጥ ማቀጣጠል ያስፈልጋል። በድህነት የተጐዳ ኅብረተሰብ ሁሌም በምሬት ውስጥ የሚኖርና ከዚህ ችግር የሚያላቅቀው ትክክለኛ አማራጭ ካልቀረበለት በስተቀር በሌሎች ፅንፈኛና መሠረተ ቢስ አማራጮች መማለሉ አይቀርም፡፡ በተለይም በምድራዊው ህይወቱ ያላለፈለትን ህዝብ 'በሰማይ ቤት ያልፍልሃልና ማንኛውንም ፅንፈኛ አቋም ፈፅም' ለሚሉ ዓይነት ቅስቀሳዎች ተጋላጭ ሊሆን ይችላል። ኋላ ቀርነትም እንዲሁ አንድን ኅብረተሰብ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እድል በመንፈግ ለተስፋ መቁረጥና ለፅንፈኝነት ሊዳርገው ይችላል። እርግጥ መንግሥት ፈጣንና ብዙሃኑን ህዝብ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትን ልማት አስፋፍቷል፡፡ መሠረተ ሰፊና አሳታፊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትም ገንብቷል፡፡ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ቀጣይ ትግል አካሂዶ በመስኩ ከፍተኛ ድሎችን አስመዝግቧል፤ በማስመዝገብ ላይም ይገኛል፡፡ በመሆኑም ዛሬ ሀገራችን ከመቼውም ጊዜ በተለየ ሁኔታ በፈጣንና ህዝብ በሚጠቀምበት ዴሞክራሲያዊ የዕድገት አቅጣጫ እየገሰገሰች ትገኛለች። ዕድገታችን ፈጣንና መሠረተ ሰፊ በመሆኑም የህዝቡን ተስፋ አለምልሟል፡፡

ዴሞክራሲያችን ብዝሃነትን በማወቅና በማክበር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በህዝቦች መካከል ፍቅርን፣ መከባበርንና መቻቻልን አጐልብቷል፡፡ በዚህም የእርስ በርስ መናቆርና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችል ተስፋ መቁረጥ መሠረቱ ተንዷል፡፡ በርካታ ሀገሮች በቀለም አብዮቶች ሲናጡና ከቀውስ ወደ ቀውስ ሲረማመዱ በሀገራችን ሠላምና መረጋጋት እንደሰፈነ ቀጥሏል፡፡ አክራሪ ፖለቲከኞቹ ሊረባበሩበት ወደሚችሉበት ስለ ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል ጥቂት እናንሳ። ወጣቱ ለሥራ አጥነት፣ ጥራት ለሌለው ትምህርት፣ ከተደራጀ ፖለቲካዊ ተሳትፎ መገለልና ለመልካም አስተዳደር የሚያመች ሁኔታ ባልገጠመው ወቅት አክራሪዎቹ ስሜት ቀስቃሽ የሆኑ አቀራረቦችን በመጠቀም በደካማ ጐኑ ለመግባት የተሻለ ዕድል ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

መንግሥት ከድህረ ምርጫ 97 ቀውስ በመማር የወጣቱን የልማትና የተጠቃሚነት፣ የመልካም አስተዳደርና የተሳትፎ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አድርጎ የተሳካ ውጤት ያገኘነውም ከዚህ መሠረታዊ እውነታ በመነሳት ነው። ወጣቱ ትውልድ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሚካሄደው ትግል ዋነኛ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎንም በመንግሥት አመራር ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች አሠራራቸውን ከኃይማኖታቸው ነፃ በሆነ እንዲከውኑ ማድረግ ተገቢ ነው። እንደሚታወቀው በልማታዊውና ዴሞክራሲያዊው መንግሥት ውስጥ የተለያዩ እምነት ተከታዮች መኖራቸው ነባራዊ እውነት ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ የግል እምነትን የማክበርና የማስከበር ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ መንግሥታዊ አገልግሎትን የመስጠት ጉዳይ ከኃይማኖት ገለልተኛ በሆነ መንገድ መካሄዱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሲሆንም የማናቸውም እምነት ተከታይ የሆኑ ዜጎች ከመንግሥት የሚያገኙት አገልግሎት በእኩልነትና ከኃይማኖት ገለልተኛ በሆነ መንገድ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

በሌላ በኩልም አክራሪዎቹንና ደጋፊዎቻቸውን ጠንቅቆ በማወቅ ሊፈጥሩ የሚችሉትን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻዎች መመከት ያስፈልጋል። ለነገሩ የአክራሪዎቹን ደጋፊዎች የሆኑትን እነ የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮንና ግብረ አበሮቻቸውን ምን ምን ማለት ይቻላል?...ጣቢያዎቹ ከመንግስታቸው የውጭ ፖሊሲ ውጭ የሚሰሩ ናቸው። መንግስታቸው አሸባሪነትን ሲያወግዝ እነርሱ ደግሞ በተፃራሪው መንገድ በመጓዝ አክራሪዎቹን ሲያንቆለጳጵሱ ይታያሉ።...ካድሬ እንዳንላቸው ጋዜጠኞች ነን ይሉናል። ጋዜጠኛ ናቸው እንዳንላቸው

ደግሞ የአክራሪዎች መልማይና አፈ-ቀላጤ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ሚናቸውን ለይተው ለምን ከወደ መረጡት እንደማይሰለፉ ለማንም ግልፅ አይደለም። እርግጥ እነዚህ ሃይሎች ሃይማኖታዊ ጭምብል ቢያጠልቁም ምግባራቸው የፖለቲከኛ መሆኑን የነሲብ ዲስኩራቸው ያሳብቃል፡፡ ለዚያውም በጥፋት መልዕክተኝነት የተሰለፉ ናቸው። እርግጥ ነው አክራሪዎቹና ደጋፊዎቻቸው ከትላንት ወደ ዛሬ የዞረ ቀሪ ሂሳባቸውን እያወራረዱ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ዋነኛ ፍላጎታቸው ያልተረጋገጠ ጉዳይን ወደ ሚዲያ ይዘው በመቅረብ ህዝብን ከመንግስት፣ መንግስትን ከህዝብ ለማቃቃር መሆኑ በግልፅ ስለሚታወቅ ነው፡፡

ይሁን እንጂ እንደ ቦይ ውኃ ወደ ፈለጉት አቅጣጫ የሚመራ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም እንደማያገኙ ግን በፍጹም እርግጠኝነት ልነግራቸው እወዳለሁ፡፡ ላለፉት ሁለት ዓመታት እነ የአሜሪካ ድምፅና የጀርመን ሬዲዮ ጣቢያዎች እንዲሁም የተለያዩ የሃይማኖት ስም በተላበሱ መፅሔቶች አማካኝነት ሙስሊሙን ማህበረሰብ ከሙስሊሙ እንዲሁም ሙስሊሙን ከመንግስት ጋር ለማላተም ሲያደቡ የነበሩ፣ ነገር ግን ያልተሳካላቸው ቀበኞች መሆናቸውን አንዘነጋም፡፡ በመሆኑም ፅንፈኞቹ እኛ የተለያዩ የልማትና የዕድገት ዓይነቶች እንጂ፤ የእምነት ‘ፋሽን’ እንዳላማረን በመረዳት በአሉባልታ ያደፈ ብዕራቸውን ከክርስትናም ይሁን ከእስልምና ሃይማኖቶች ላይ እንዲያነሱ በግልፅ ሊነገራቸው ይገባል። የኃይማኖት እኩልነት ጨርሶ በማይታሰብባት፣ የዜጎች መብትና ነጻነት ቅንጦት ተደርገው በሚቆጠሩባት፣ ጥቂቶች እንዳሻቸው በሚፏልሉባት ሀገር ኢትዮጵያ ዛሬ ያ ሁሉ ቀርቶ ሕዝቦች ያፈቀዳቸውን እምነትና አመለካከት ማራመድ፣ ሰብዓዊ ክብራቸው ተጠብቆ መንቀሳቀስ የቻሉባትን አዲሲቷ ኢትዮጵያን በመፈቃቀድ መሥተው በእኩል ተጠቃሚነት ኑሯቸውን መግፋት ጀምረዋል፡ ይህ ከቶ እንዲቀለበስ አይሹም፤ ኃይማኖትንና ፖለቲካን ደበላልቀው ማቡካት የሚሹትንም እዚያው በፀበል ይላቸዋል፡፡